# ለቴዲ አፍሮ የአዲሱ ዓመት (፳፻፩ ዓ.ም.) የመልካም ምኞት መግለጫዎች

*ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ (የአንድነት ሊቀመንበር)፣ አቶ ስዬ አብርሃ፣ አትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገ/ሥላሴ፣ አቶ ቡልቻ ደመቅሳ (የኦፌዲን ሊቀመንበር)፣ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ (የቀድሞ የኢፌዲሪ ፕሬዝዳንት)፣ ፈለቀ ኃይሉ (በአአዩ የያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት መምህር)፣ … እንዲሁም የተለያዩ የኅብረተሰቡ ክፍሎች ልባዊ የመልካም ምኞታቸውንና የእንኳን አደረሰህ መልዕክታቸውን ሀገር ውስጥ በሚታተመው "እንቢልታ" ጋዜጣ ላይ አስተላልፈዋል።*

## "መጪው ዓመትም የኢትዮጵያን ህዝብ የምታስደስትበት እንዲሆንልህ እመኛለሁ!"

በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሥራ ቆይታዬ ወቅት፣ የኢትዮጵያ የሕግ መረብ ሻርኩንም፣ ዶልፊኑንም እያጠመደ ለእስር ሲዳርግ ስመለከት፣ ይህ ዕጣ ፈንታ ለጋዜጠኛው፣ ለፖለቲከኛው፣ ለነጋዴው፣ ለሌላውም፣ ለሌላውም … በየተራ መዳረሱን ሳስተውል "ሰዎች ይኼ ነገር ወደ እኛም መምጣቱ አይቀርም" እያልኩ ከሥራ ባልደረቦቼ ጋር እቀልድ ነበር። ቀልዴ ቀልድ ሆኖ አልቀረም እኔም የድርሻዬን አነሣሁ፤ ዛሬ ደግሞ አዲሱ ባለሣምንት (ባለተራ) የኢትዮጵያውያን የሠላም፣ የእርቅ፣ የፍቅር ጉጉት ወደ ድንቅ ዜማ የለወጥክልን ቴዲ አፍሮ ነህ።

አምና ይኼን ጊዜ የአንተ "አበባየሆሽ" በመላው ኢትዮጵያ እንዲሁም ኢትዮጵያውያን በተበተኑበት የዓለም ክፍል ሁሉ ተስተጋባ። ከአንተ ጋር አዚመን፣ የሀገራችንን ከውድቀት መነሣት ተመኘን (ሠለሞን አለ ጊዜ ለኩሉ፤ ይሰግድልሻል የናቀሽ ሁሉ እያልን)። በዘንድሮው ዓመትም ይህ ብዙ የተቀየረ አይመስልም። ይህቺን መልካም ምኞት ስጫጭር እንኳን ከርቀት የምሰማው ቅላፄ ያው የአንተ አበባየሆሽ ነው። ዛሬም እናደምጠዋለን፤ ከኀዘን ቀላቅለን እናዜመዋለን፤ አንተ በሙዚቃ መድረክ ሳይሆን በቃሊቲ አጥሮች ተወስነኸልና።

ቴዲ በዓል በቃሊቲ በብዙ ድብልቅልቅ ስሜት የታጀበ እንደሆነ አውቃለሁ ጓደኞችህን፣ ቤተሰቦችህን፣ የበዓሉን አጀብ ሁሉ በደንብ ትናፍቃለህ። ከሌላው ቀን ሁሉ የዛን ዕለት በጣም እስረኛ ነህ። በሕይወትህ ተሰምቶህ የማያውቁ ስሜቶች በየቀለማቸው ይጐበኙሃል። አንድ ነገር ግን እርግጠኛ ነኝ፤ ይኼ ሁሉ የኀዘን ጐርፍ እና የምታልፍበት ጐርበጥባጣ መንገድ ከድብታችን የሚያነቃን፣ በተስፋ የሚያሻግረን ኢትዮጵያውያንን ሁሉ የሚያያይዘን ሌላ ውበት፣ ሌላ ዜማ ያስፈጥርኻል እንጂ አንተን የእኛን ልጅ ሊሰብርህ አይችልም። መጪው ዓመትም በዚህ አዲስ ክብር፣ የኢትዮጵያን ህዝብ የምታስደስትበት እንዲሆንልህ እመኛለሁ፤ ቴዲ የሀገሬ አብሪ ኮከብ፣ የዛሬ ዓመት በግዮን ያገናኘን።

*አክባሪህ እና አድናቂህ*

*ብርቱካን ሚደቅሳ*

## "እግዚአብሔር ጽናቱን ይስጥህ!"

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ፣ የኢትዮጵያን የፍትህ ሥርዓት መውደቅ ማጥናት ለሚፈልግ ሰው ጥናቱን በኢትዮጵያ እስር ቤቶች ቢጀምር በአንድ ጊዜ ብዙ ለማወቅ ያስችለዋል። ብዙ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች አነግ ናችሁ ተብለው እስር ቤት ታጉረዋል፤ ብዙ ንፁኀን ዜጎች ወንጀል ሠርታችኋል ተብለው ጥፋተኛ መሆናቸው ሳይረጋገጥ ሰባትና ስምንት ዓመታት እስር ቤት ታጉረዋል።

ብዙ ዓመታት ታስረው ቤትና ንብረታቸው፣ ቤተሰባቸው ከፈረሰ በኋላ ነፃ ናችሁ ተብለው የሚፈቱ አሉ። በተለይ አዲስ ዓመት ሲመጣ ደግሞ ፍትህ እንኳን ባይገኝ ድንገት የባለሥልጣኖቹ ልብ ተከፍቶ ይቅርታ፣ ምህረት ይወርድልን ይሆን ብለው በተስፋ የሚጠባበቁ አሉ። እኔም የባለሥልጣኖቹ ልቦና ተከፍቶ፣ ምህረትና ይቅርታ ወርዶ፣ ፍትህ ተቆልፎባቸው ያሉት ወገኖቻችን ነፃነታቸውን አግኝተው ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንዲቀላቀሉ እመኛለሁ፤ ለሁሉም መልካም አዲስ ዘመን እመኛለሁ።

ስድስት ዓመት ታስሬያለሁ፤ ስድስት አዲስ ዓመታት እስር ቤት ውስጥ አክብሬያለሁ። አብዛኛዎቹን የእስር አዲስ ዘመኖች ያሳለፍኳቸው ከወንድሜ አቶ ታምራት ላይኔ እና ከአቶ ሙኒር ዩሴፍ ጋር ለብቻ በታሰርንበት ልዩ የጥበቃ ክፍል ነው። እነዚህ ወንድሞቼ ከቤተሰባቸው ጋር እንዲቀላቀሉ እመኝላቸዋለሁ፣ ቤቴ ሆኜም አስባቸዋለሁ። እኛ ከነበርንበት ልዩ ጥበቃ ክፍል፣ በአንድ አጥር ከኛ ተለይቶ ሻለቃ ፀሐዬ ወ/ሥላሴ ነበር፤ አቶ ክንፈ ገ/መድህን በመግደሉ፤ እሱም ሞት ተፈርዶበት በሕይወት የለም፤ የአቶ ክንፈንም፣ የሻለቃ ፀሐዬንም ነፍስ እግዚአብሔር በገነት እንዲቀበል እፀልይላቸዋለሁ።

በዛች ሻለቃ ፀሐዬ በነበረባት በጣም ጠባብ ቤት ገብቶ የሚገኘው ቴዎድሮስ ካሳሁን እንደሆነ ሰምቻለሁ። አምና ለኢትዮጵያ ህዝቦች ፍቅር፣ መተሳሰብ እና እርቅ ብለህ ጅማ ድረስ ዘልቀህ ያከበርከውን የዘመን መለወጫ ዓይነት የእርቅ፣ የፍቅር፣ የአንድነት መልዕክትህ እንደገና ለኢትዮጵያ ህዝብ የምታስተላልፍበት አዲስ ዘመን እንዲመጣልህ እመኝልሃለሁ፤ እግዚአብሔር ጽናቱን ይስጥህ! እግዚአብሔር ይጠብቅህ! እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይጠብቅ! - አሜን!!!

***አቶ ስዬ አብርሃ***

## “ከተከሰሰው ክስ ነፃ ሆኖ አዲስና ጥሩ ነገር እንዲሠራ እመኛለሁ”

ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) የምንወደው ዕንቁ አርቲስት ነው፤ በዚህ አዲስ ዓመት ከተከሰሰበት ክስ ነፃ ሆኖ፣ በሚቀጥለው ዓመት አዲስና ጥሩ ነገር እንዲሠራ እመኛለሁ። በተለይ ደግሞ ለእኛ ከእስር ተፈቶ እንድናየው እንፈልጋለን።

***አትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገ/ሥላሴ***

“ቴዎድሮስ ከሳሁን በወጣትነቱ ሠላምና ፍቅርን የሰበከ፣ የኢትዮጵያ ውድ ልጅ ነው። 2001 ዓ.ም. የአርቲስት ቴዲ አፍሮ ፍርድ በትክክል ተፈርዶ፣ ከእስር ነፃ ሆኖ እንዳየው እመኛለሁ። “

***አቶ ቡልቻ ደመቅሳ***
***የኦፌዲን ሊቀመንበር***

“የ2001 ዓ.ም. አዲስ ዓመት በጣም ሳይርቅና ሳይዘገይ፣ አርቲስት ቴዎድሮስ ካሳሁን፣የፖለቲካ እስረኞች እና ሌሎችንም ጨምሮ ፍትህ ላላገኙ እስረኞች ፍትህ እንዲያገኙ መልካም ምኞቴን እገልጻለሁ።”

***ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ***
***የቀድሞ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፕሬዝዳንት***

## አሁን ላለው ትውልድ አርአያ ነው

እውነቱን ለመናገር ቴዲ እዚህ ሙያ ውስጥ ከገባ ጀምሮ በጣም ነው የማደንቀው። የመፍጠር ብቃቱ፤ ውስጡ ያለውን ነገር የመግለጽ ድፍረቱ በአጠቃላይ ለዚህ ሙያ የተፈጠረ የዘመኑ ብርቅዬ ሙያተኛ ነው ማለት ይቻላል። ቁጭ ብለን እንዲህ በምንወያይበት ወይንም በምንጨዋወትበት ጊዜ፣ በተፈለገው ጉዳይ ርዕስ ተሰጥቶት እዚያው ተቀምጦ ወዲያውኑ ዜማም ሆነ ግጥም መድረስ የሚችል እንዲሁም የቅንብር ሃሣብ የማመንጨት ብቃት ያለውና በዚህ ላይ ብዙ ነገር መሥራት የሚችል ኀበዝ ድምፃዊ ነው። ለዚህም ነው አሁን ላለው ትውልድ አርአያ ነው ወይንም ታሪክ ሠሪ ነው ብዬ የማምነው።

ቴዲ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የሚሠራቸው ሥራዎች ፈር ቀዳጆች ናቸው፤ የቴዲን ዘፈን ያልሰማንበት ወቅት የለም። በዚህ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንኳ በሀገራችን የቦብ ማርሌን 60ኛ ዓመት በዓል ሲከበር፣ አትሌቶቻችን ድል ሲያደርጉ ብቻ በተለያዩ አጋጣሚዎች በእኛ ሕይወት በአጠቃላዩ ከሀገራችን ጋር የተያያዙ ሥራዎችን እየሠራ ያለ ወጣት ነውና አደንቀዋለሁ። ለቴዲ አፍሮ ያለኝ አክብሮትና ፍቅር ከፍተኛ ነው፤ ለሞያው ብቃት ትልቅ አክብሮት አለኝ። ሠላምና ጤናውን እመኝለታለሁ፤ ነፃ ወጥቶ አዳዲስ ሥራዎቹን እንደምናዳምጥ ተስፋ አደርጋለሁ።

*ፈለቀ ኃይሉ*

*በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት መምህር*

## ”ይህም ያልፍ ይሆናል”

ቴዲ እንኳን ለአዲሱ ዓመት አደረሰህ! አንተ ለኔ ዘፋኝ ብቻ አይደለህም፤ የሠላም ሐዋርያ ጭምር እንጂ። በዘፈኖችህ ስለሠላም፣ ስለይቅር ባይነት፣ ስለፍቅር፣ ስለሀገር አንድነት ሰብከሃል። የሚያሳዝነው አንተ ፍቅርን፣ ሠላምን፣ ይቅርታን ተነፍገህ ከአምስት ወር በላይ እስር ቤት መክረምህ ነው።

ቴዲ ኢትዮጵያዊ የተፈጠረው አንተ ከደረሰብህ ፈተናም ለባሰ ፈተና ነውና ብዙም ኀዘን አይግባህ። አዕምሮን በሚከብዱ ኀዘኖች መፈተን የኢትዮጵያዊ ብቸኛ መለያው ነውና። ስደት፣ እስር፣ ረሃብ፣ እንግልት፣ ሙስና ከኢትዮጵያ ተለይቶ ያውቃልን? በጭራሽ!

ለምሣሌ ረሃቡን ውሰድ፤ ወገኖቻችን በየአቅጣጫው እያለቁ ነው። በእንዲህ ዓይነቱ ዘግናኝ ዜና ተከበን አዲስ ዓመትን በደስታና በፈንጠዝያ ማሳለፍ እንደምን ይቻለናል? እንኳን የወገንህ በፀና ረሃብ ማለቅ ይቅርና የጎረቤትህ የዕለት መከፋት በዓላትህን ወደ ኀዘን እንደሚለውጡት ስታስብ ጭንቀትህን ያከብደዋል።

ቴዲ ለዚህ ህዝብ የተፈጠረ ምድራዊ የማፅናኛ ቃል ያለ አይመስለኝም፤ መታመኛችን አንድ ፈጣሪ ነው፤ ”ይህም ያልፍ ይሆናል” ካላልን በስተቀር ሌላ መጽናኛ ቃል የምናገኝ ዓይነት አይደለንም።

”አስጨናቂው በከበረ ነገርዋ ሁሉ ላይ እጁን ዘረጋ።” ይላል መጽሐፍ ቅዱስ። አስጨናቂዋ ለበዛ ለእንደኛ ዓይነቷ ምስኪን ሀገር ደግሞ ያላት ብቸኛ ዕድሜ መግፊያ ቃል አንድ ነው፤ ”ጌታ ሆይ ይህም ባንተ ይለፍ!” ቴዲ ያንተም የዘወትር ጸሎት ይህ ይሁን፤ ”ጌታ ሆይ ይህም ባንተ ይለፍ!”

*መዝሙረ ሠሎሞን (ከብሥራተ ገብርኤል)*

## ”በያዝነው ጾም በዱዐ እናስብሃለን”

ቴዲ አይዞህ በርታ! አላህ ካንተ ጋር ይሁን! በዚህ በያዝነው ጾም በዱዐ እናስብሃለን። ”ሃቅ የእነርሱ የሆነች ሰዎች አያፍሩም”፤ አይዞህ ወንድማችን! አላህ ከተበደሉ ሰዎች ጎን ይቆማልና ብዙም ኀዘን አይግባህ።

*ሰይድ አብዱልሰላም (ከአዲሱ ገበያ)*

## “ከእስር ቤት ትልቅ ጽናት እንደምትማር ይሰማኛል”

ቴዲ እንኳን ለአዲሱ ዓመት አደረሰህ! እኛ በዓላትን በአንተ ዘፈኖች እያደመቅን፣ አንተ እስር ቤት ማሳለፍህ ደስታችንን ጎዶሎ አድርጎታል። ቴዲ የእስር ቤት ኑሮ ምን ይመስል ይሆን? እንኳን እስር ቤት መግባት ይቅርና ለሥራ ራቅ ያለ ሀገር በመሄድ ከቤተሰብ አባላት በበዓላት ቀን መጉደል፣ ምን ያህል ቅር እንደሚያሰኝ የምናውቀው ነው። ቴዲ አንተስ ምን ተሰምቶህ ይሆን? ቤተሰቦችህስ በምን ዓይነት ኀዘን ላይ ይሆኑ?

ቴዲ ከዚህ ከእስር ቤት ሕይወት ትልቅ ጽናት እንደምትማር ይሰማኛል። ብልሆች እንግልትን የመማሪያ ት/ቤት አድርገው ያልፉታል፤ ሌሎች ግን ተስፋ መቁረጥን ገንዘባቸው ያደርጉበትና ይጠፉበታል፣ ቴዲ የማያልፍ ቀን የለምና አንተም ከዚህ ሕይወት ታላቅ ብርታትን ተማር። ፈጣሪ የሰው አዕምሮ ሊሸከመው ከሚችለው በላይ ፈተናን አልፈጠረምና አይዞህ ቴዲ በርታ! እግዚአብሔር ካንተ ጋር ይሁን። ለቤተሰብህም እግዚአብሔር መፅናናትን ይስጣቸው።

*አድናቂህ ማሕሌት ነጋሽ (ከፈረንሳይ ለጋሲዮን)*

## “የዛሬ ዓመት አስጨፍረኸን ነበር”

እንኳን ለአዲሱ ዓመት አደረሰህ ቴዲ! ለአንተ ያለኝ አድናቆትና ክብር ብዕር እንዳነሳ አደረገኝ እንጂ የብዕር ሰው ሆኜ አይደለም። ቴዲ እስር ቤት ከተወረወርክ አምስት ወር ተቆጠረ፤ በነዚህ በአምስት ወራት ውስጥ ግን እኛም ስላንተ መስማት፣ የተጻፉ ነገሮችን ከማንበብ አልቦዘንም።

የዛሬ ዓመት የአዲስ ዓመት መቀበያ ምሽት አስጨፍረኸን ነበር፤ ዛሬ ግን ከጎናችን አለመኖርህ በእጅጉ አሳዝኖናል፣ ቴዲ እንወድሃለን። ያለ አንተ አዲስ ዓመት አሮጌ ነው፤ አዲስ ዓመትን በደስታ እንቀበለው ብንል እንኳ በፍፁም አንችልም። ምክንያቱም በቀን ቢያንስ ቢያንስ ሁለቴና ሦስቴ ያንተን የአዲሱ ዓመት መቀበያ ሙዚቃ (”አበባየሆይ”) በራዲዮ እየሰማን ነውና።

ቴዲ አንተ እኮ ያለኸው እስር ቤት ነው፤ እኛ ግን እቤታችን። ቴዲ አዲስ ዓመቱን እስር ቤት ”ሀ” ብለህ ልትጀምር ነው፤ ልልህ የምችለው በርታ! ጽናቱን ይስጥህ ብቻ ነው፤ እግዜር ካንተ ጋር ይሁን!

*ፍቃዱ ተሰፋዬ (ከመነን)*